# መጨረሻ ላይ ስምምነት !!

***ግሎባላይዜሽንን አማራጭ የሌለው ነው ብለው ሲሰብኩ የነበሩ የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶች ጥያቄ ውስጥ እያስገቡት ነው።ክርክር እንዲፈጠር የግዴታ በሩን ከፍተዋል። ከፕሮፌሰር ዳኒ ሮዲክ-የሀርባርድ ፕሮፌሰር***

እ.አ. በ1914 ዓ.ም በወርቅ ላይ የተመሠረተው የገንዘብ መሸከርከር(Gold-Standard) ሲናጋ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ የሆኑት ዓለም አቀፍ ንግድና የካፒታል መንቀሳቀስ በአንድ ጊዜ ይቆማሉ። በአገሮች መሀከል ይካሄድ የነበረው ንግድና የመዋዕለ-ነዋይ ተግባራዊ መሆን ያከትማሉ። በያዝነው ዘመን እንደዚህ ዐይነቱ የዓለም ኢኮኖሚ መናጋት እንደገና ይከሰት ይሆን ?

በአለፉት ሃያና ሰላሳ ዐመታት ግሎባላይዜሽን ለብዙ አገሮች ዕድገትን እንዳመጣ የማይታበል ሀቅ ነው።በተለይም በቻይናና በተቀሩት የአሺያ አገሮች የታየው የኢኮኖሚ ዕድገት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች ከድህነት መላቀቅ ከግሎባላይዜሽንና ከዓለም ንግድ እንቅስቃሴና ከካፒታል መሸከርከር ጋር የተያያዘ ለመሆኑ ግልጽ ነው። ይሁንና ይህ ዐይነቱ መጠኑ ሰፊ የሆነ የእቃዎችና የካፒታል እንቅስቃሴ በእርግጠኛ መሰረት ላይ እንዳልቆመ እየታየ ነው። በየአገሩ ባሉት ኢንስቲቱሽኖችና የህግ ተቋሞች ላይ ከሚመካው የብሄራዊ ኢኮኖሚ ይልቅ በተለያዩ የኢኮኖሚ መሳሪያዎች እርማት ሊደረግለት የማይችለው ግሎባላይዜሽን አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ይገኛል። በዓለም አቀፍ የሚንቀሳቀሱትን ኩባንያዎች የሚቆጣጠር ዓለም አቀፋዊ ኢኮኖሚ መስሪያ ቤት(Cartel Office) ፣ የመጨረሻ መጨረሻ የብድርን መጠንና የገንዘብን እንቅስቃሴ በልዩ ልዩ መሳሪያዎች የሚገታና የሚቆጣጠር ዓለም አቀፋዊ ባንክ ፣ የዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን የሚቆጣጠርና እንዲሁም ደግሞ የግሎባል ኢኮኖሚን መተሳሰር የሚከታተል( Global Net Work) ፣በተጨማሪም ዓለም አቀፋዊ ዲሞክራሲ ስለሌለ ፣ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። በሌላ አነጋገር የዓለም ገበያ እጅግ ደካማ በሆነ የአስተዳደር መዋቅር ላይ በመቆሙ በዓለም ህዝቦች ዘንድ ተቀባይነትን እያጣ በመምጣቱ ሊፈረካከስ ይችላል።

## በጣም ብዙ ችግሮች ፣ እያደገ የመጣ ተቃውሞ!!

አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው ኢኮኖሚያዊ ፣ በተለይም የፊናንስ ቀውስ ጥያቄውን እያከረረው ነው። በሰሜን አሜሪካ የሚካሄደው የፕሬዚደንትነት ውድድር አዳዲስ ጥያቄዎች እንዲነሱ በማድረግ ልቅ የሆነ ነፃ የዓለም ንግድ ተቀባይነት እንደሌለው እያረጋገጠ ነው። በዓለም አቀፍ የሚንቀሳቀሰውን ካፒታልና(ገንዘብ) በልዩ ልዩ መልክ የሚገለጸው በተጨባጭ ኢኮኖሚ ላይ የማይፈሰው መዋዕለ-ነዋይ የሚቆጣጠር ልዩ ዐይነት መስሪያ ቤትና መሳሪያ(መካኒዝም) ባለመኖሩ ተፈጥሮአዊ የውስጥ ድክመት የሚታይበት የፊናንስ ገበያ ሰሜን አሜሪካ በተከሰተው በብድር በተሰሩ ቤቶች ቀውስ ምክንያት በመናጋት ላይ ይገኛል። በልዩ ዐይነት ዓለም አቀፋዊ ድጎማ የማይደገፈው የእህል ዋጋ መወደድ ፣ ልቅ የዓለምን ንግድ እንቅስቃሴ ደካማነት እያጋለጠው በመምጣት „በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ“ እንዲሉ የአየር መበረዝ ታክሎበት ፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ የአየሩ የሙቀት መጠን መጨመርና በብዙ አካባቢዎችም ድርቅ መከሰት ፣ በዓለም ገበያ ላይ የሚቀርበውን የእህል መጠን እየቀነሰው መጥቷል።

በዚህ መልክ ግሎባላይዜሽን አደጋ ላይ ከሆነ ዋና ጠላቶቹ ማናቸው ? ድሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሳሰረውን ንግድና ግሎባላይዜሽንን የሚያራምደው ኤሊት የግሎባላይዜሽን ዋና ጠላቶች ናቸው ብሎ የሚያስባቸው አናርኪስቶች ፣ በራሳቸው ፍላጎት ብቻ የተጠመዱ ጭፍኖች ፣ የሰራተኛው የሙያ ማህበሮችና ተምኤታውያን እንዲሁም ግራ የተጋቡ ወጣቶች ናቸው ተብሎ ይታመን ነበር። የግሎባላይዜሽን አራማጅ ኤሊቶች ግን

እነሱ ብቻ ዕውነተኛ ተራማጆች ፣ ድህነትን ለማጥፋት ቆርጠው የተነሱና ለዚህም ደግሞ ፍቱን መሳሪያ እንዳላቸው እርግጠኝነት የሚሰማቸው ነበሩ።

ይህ እርግጠኝነትና በራስ መተማመን በአሁኑ ወቅት እንዳለ ደብዛው በመጥፋት ላይ ነው። እንደዚሁ ድሮ በየመንገዱ ላይ የሚታየው ፀረ-ግሎባላይዜሽን እንቅስቃሴ በአሁኑ ወቅት ተዳክሞ ይገኛል። በአሁን ወቅት ጎልቶ የሚታየው ድሮ ሽንጡን ገትሮ የሚታገለው የግሎባላይዜሽን አራማጅ ኤሊት የራሱን መፈክር ጥያቄ ውስጥ ሲያስገባ ነው።

ከነዚህ ውስጥ ለዩኒቨርሲቲ መማሪያ የሚሆኑ የኢኮኖሚ መጻህፍት ያዘጋጀው ፕሮፌሰር ሳሙኤልሰን ፣በአሁኑ ወቅት የቻይና መጠናከርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተዋናይ መሆንና የአሜሪካንን ጥቅም መጻረር እንዳሰሰበው ሲጽፍ ፣ ግሎባላይዜሽን አሜሪካንን እየጎዳ ለመሆኑ ያመለክታል። እንደዚሁም የውጭ ንግድንና የዓለም አቀፍ የስራ ክፍፍልን ጠቃሚነት አጥብቆ በመጽሀፍቶቹ የሚያነሳው ፕርፌሰር ክሩግማን የተባለው ኢኮኖሚስት ከሶስተኛው ዓለም አገሮች ጋር የሚደረገው የንግድ ልውውጥ በዚህ ከቀጠለ አሜሪካንን ሊጎዳ እንደሚችል ያሳስባል። በሌላ አነጋገር ፣ በዚህ ዐይነቱ ልቅ ነፃ የውጭ ገበያ ንግድ አማካይነት የአሜሪካ የውስጥ ምርት ሂደት እጅግ እየተዳከመ ነው። አላን ብሊንደር የተባለው የድሮው የፌዴራል ባንክ ምክትል ሀላፊ ከአሜሪካ እየወጣ ወደ ሌሎች አገሮች የሚተከለው ኢንዱስትሪ(out sourcing) የአሜሪካንን ወዝአደር ከስራ መስኩ እያፈናቀለ እንደመጣ ያመለክታል። ማርቲን ዎልፍ የተባለው በየጊዜው ለፋይናንሺያል ታይምስ ጽሁፍ የሚያቀርብና አጥብቆ ግሎባላይዜሽንን የሚያራምድ ፣ በአሁኑ ወቅት የፊናንስ ገበያ ትርምስ ውስጥ እንዳለና አሉታዊ ውጤቱም አደገኛ እንደሆነ ያደረበትን የመንፈስ መረበሽ በይፋ ይናገራል። የቀድሞው የፕሬዚደንት ክሊንተን የገንዘብ ሚኒስተርና „ሚስተር ግሎባላይዜሽን“ ተብለው የሚጠሩት ላርይ ሰመርስ በዓለም ገበያ ላይ የሚደረገው ውድድርና ሽቅድምድሞሽ እንዳላስደሰታቸውና የግዴታ የየአገሮች መንግስታት ቁጥጥር መኖር እንዳለበትና ለሰራተኛውም አንድ ተቀባይነት ያለው ዝቅተኛ መለኪያ(minimum standard) መዘጋጀትና ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ያሳስባሉ።

እንደዚህ ዐይነቱ በአንድ ወቅት ግሎባላይዜሽንን ከሚያራምዱት የሚሰነዘረው ቅሬታ እነ ፕሮፌሰር ስትግሊትዝ ከሚጽፉት ጋር ሊወዳደር ባይችልም ፣ አንድ ርምጃ እንደሆነና መደገፍም አለበት። ትልቅ ምሁራዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ነው።ከዚህ በተረፈ አሁንም ቢሆን ተስፋ ባልቆረጡት የግሎባላይዜሽን አራማጆች ዘንድ ግሎባላይዜሽን ወዴት እንደሚያመራ ለመገመትና ቁርጥ ያለ ውሳኔ ለመውሰድ ከፍተኛ አለመግባባት እንዳለ ይታያል። በመሀከላቸው ከፍተኛ ትርምስ እንዳለ በየጊዜው ከሚያወጡት ጽሁፍ ለማንበብ ይቻላል።

## <u>አዲስ ህግን የመፈለግ ችግር</u>

ነፃ ንግድን አጥብቆ የሚያራምደው ያግድ ባግህዋቲ የሚባለው ኢኮኖሚስትና የግሎባላይዜሽን ጓደኞች ኢንስቲቱት ዳይሬክተር የሆነው ፍሬድ በርግሰተን በበኩላቸው ግሎባላይዜሽንን በጥያቄ ውስጥ የሚሰያስቀምጡትን ከጥቅሙ ይልቅ ችግሩን አጉልተው እንደሚያነሱ ያመለክታሉ። ይሁንና በሁለቱ መሀከል የሚደረገው ክርክር ደግሞ የሚያመለክተው በመሀከላቸው ትልቅ አለመግባባት እንዳለ ነው።ለምሳሌ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚደረገው የንግድ ስምምነት ይልቅ በአካባቢዎች(regions) መሀከል የሚካሄደውን የንግድ ልውውጥና ስምምነት በርስተን ሲደግፍ ፣ ባግህዋቲ ደግሞ ይህንን ዐይነቱን ስምምነት ይቃወማል። ያም ሆነ ይህ ግሎባላይዜሽንን ጥያቄ ውስጥ እያስገቡ የመጡ የኢኮኖሚ ምሁሮች በምንም ዐይነት ግሎባላይዜሽንን መቃወማቸውን አያመለክትም። የነሱ ዋና ፍላጎት በአንድ በኩል ግሎባላይዜሽን በእርግጠኛ ኢንስቲቱሽናዊ መሰረት ላይ የሚቆምበትን ዘዴ መፈለግ ሲሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በአገራቸው ውስጥ በግሎባላይዜሽን አማካይነት የሚጎዳው ሰራተኛ በልዩ የመካካሻ ድጎማ ብሶቱን ለማብረድ ነው። በዚህም ምክንያት የሚሰነዘሩት አስተሳሳቦች ገና መስመር ያልያዙና ጥራት የሌላቸው ናቸው። ግሎባላይዜሽንን አስመልክተው በየጊዜው የሚያቀርቡት ጽሁፎች ክርክሩ እንዲጦፍ በር ከፍቷል። ስለዚህም ግጭቱ ከመንገድ ላይ ወጥቶ በወረቀት ላይ የሚደረግ ፍጥጫ ሆኗል።

እዚህ ላይ ነው የግሎባላይዜሽን ተከታዮችና አራማጆች መረዳት ያለባቸው። ከዚህ ቀደም ግሎባላይዜሽንን በመቃወም የሚደረገው ሰላማዊ ሰልፍም ሆነ የሚቀርበው ትችት አናርኪስቶች የሚባሉት ዝምብለው ከሆዳቸው አውጥተው የሚሰነዝሩት ነገር ሳይሆን በእርግጥም ጠንቁ ስላሳሰባቸው ነው። ከዚህ ስንነሳ ዛሬ የሚነሳው ጥያቄ ግሎባላይዜሽንን ይደግፋሉ ወይስ ይቃወማሉ ብሎ የምርጫ ጥያቄ የማቅረብ ጉዳይ አይደለም። የሚነሳው ጥያቄ ግሎባላይዜሽንን በምን ዐይነት ህግ መቆጣጠር ይቻላል የሚለው ነው። ዛሬ

ግሎባላይዜሽንን የሚቃወሙት በአንድ ወቅት ዲንጋይ የሚወረውሩት ሳይሆኑ በከፍተኛ ዕውቀት የሚንቀሳቀሱና የነሱን ብሶት የራሳቸው ያደረጉ ምሁሮች ናቸው።

ግሎባላይዜሽን ዘላቂነት ወይም ተቀባይነት እንዲኖረው ከተፈለገ ምሁራዊ ስምምነት ያስፈልጋል። የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ከምን ጊዜውም በላይ አዲስ ጆን ኬይነስን ይጠባበቃል።

ፕሮፌሰር ዳኒ ሮድኒክ በሀርባርድ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚ ፕሮፌሰር ሲሆኑ ፣ ይህ ጽሁፍ የቀረበው www.project-syndicate.com ለሚባለው ድህረ-ገጽ ሲሆን ወደ ጀርመንኛ ተተርጉሞ ፋይናንሺያል ታይምስ ከሚባለው የዕለት ጋዜጣ ላይ የተወሰደ ነው። ታትሞ የወጣው በ24.7.2008 ነው።

ተርጓሚው ፈቃዱ በቀለ

## የዚህ ጽሁፍ ተርጓሚ አስተያየት

ከሁለት ወር በፊት ስለግሎባላይዜሽን ያወጣሁትን ጽሁፍ አስመልክቶ ብዙ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ቀርበውልኛል። ለአንዳንዶቹ አጠር አጠር ያለ መልስ ለመስጠት የሞከርኩ ቢሆንም ፣ ብዙ ጥያቄዎች ተንጠልጠለው እንደቀሩ ይገባኛል። በመጀመሪያ ለቀረበልኝም ጥያቄ ሆነ ገንቢ ትችት ከፍተኛ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ።

አንዳንዶች ግሎባላይዜሽን እንዴት ለኢትዮጵያ ሊጠቅም ይችላል? የሚል ጥያቄዎች ሲሰነዘሩ ፣ በተጨማሪም እንደ ኢትዮጵያ ያለች ዘላለም ተመጽዋች ሃገር የዓለም ኢኮኖሚ ከሚያደርግባት ጭነት እንዴት ለመላቀቅና ራሷን ለመቻል ትበቃለች? የሚል ነው።

በእኔ ግምት ግሎባላይዜሽንን ከሚቃወሙም ሆነ ከሚደግፉ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚሰነዘሩት ትችቶች ትንሽ ከታሪክ ጋር ለማገናዘብ ያልቻሉ ናቸው ብዬ ብናገር ወደ መጥፎ ነገር እንደማይተረጎምብኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

በመጀመሪያ ደረጃ የዛሬው ዐይነት ግሎባላይዜሽን የበላይነቱን ከመያዙ በፊት በየአገሮች መሀከል በንግድ አማካይነት ግኑኝነትና የባህል ልውውጥ እንደነበር ይታወቃል። ኢዮን በሚባለው በግሪክ ደሴት ከአምስት መቶ ዐመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ብቅ ያለው ስልጣኔና የኋላ ኋላ ለግሪክ ስልጣኔ በር የከፈተው ዕድገት በዚያን ጊዜ ከነበረው ከግብጽ ስልጣኔ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነበር። እንደዚሁም በባቢሎን የነበረው ስልጣኔ ለግሪኩ አስተዋፅኦ አድርጓል። የግሪክ ስልጣኔ ካደገና ከተስፋፋ በኋላ በተለያዩ አቅጣጫዎች በአረቦችና በአይሁዲዎች አማካይነት ወደ ማዕከለኛው አውሮፓ የገባውና ለሬናሳንሰ መነሻ የሆነው በዚህ ባልተቋረጠ የህዝቦች የርስ በርስ ግኑኝነት አማካይነት መሰረት ነው። ከአስራምስተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የሩቅ ንግድ ሲስፋፋና ሲዳብር በአውሮፓ ውስጥ የአስተሳሰብና የአመራረት ለውጥ ሊታይና ካፒታሊዝም ሊያድግ የቻለው በዚህ ዐይነት የንግድና የባህል ልውውጥ አማካይነት ነው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ማለት ይቻላል ፣ በንግድም ሆነ በሌሎች ነገሮች በህዝቦች መሀከል ይደረግ የነበረው ግኑኝነት ለስልጣኔ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የታሪክን ማህደር ላገላበጠ አንድ ሃገር ወይም አንድ ህዝብ በራሱ ብቻውን ተነጥሎ ታሪክ የሰራበት ወቅትና ሃገር የለም። ህብረተሰብአዊና ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የነበሩና ወደፊትም የሚኖሩ ናቸው።

ይህ የቀድሞው ዐይነት ግሎባላይዜሽን ከ16ኛው ክፈለ-ዘመን ጀምሮ መልኩን እየቀየረና በአሸናፊዎችና በተሸናፊዎች መሀከል የሚደረግ የሞት የሽረት ትግል እየሆነ መጥቷል። ከ16ኛው ክፍለ-ዘመን ወዲህ በአውሮፓ ምድር ህብረ-ብሄሮች ሲመሰረቱና በእነዚህ አገሮችም መሀከል ውድድር ሲገባ እንደ አፍሪቃ የመሳሰሉት አህጉሮች የግዴታ ወደ ባርያ ሽያጭና የኋላ ኋላ ደግሞ ወደ ጥሬ-ሀብት አምራችነት ብቻ እየተገፈተሩ መጡ። ይህ ዐይነቱ አንድ ወጥ እንቅስቃሴ ግን እንደ አውሮፓው ዐይነት ለአፍሪቃ

ስልጣኔና ዕድገትን ከማምጣቱ ይልቅ የዕድገትን ፈለግ ያሳሳተና የህብረተሰብን ግንባታ ያጨናገፈ ፣ ለምዕራብ አውሮፓ ደግሞ ያመቸ የግሎባል ኢኮኖሚ የመጀመሪያው እንቅስቃሴ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፣ ከ16ኛው ክፍለ-ዘመን በፊት አነሰም በዛም ለስልጣኔ አመቺ የነበረው የአገሮች የንግድና የባህል ልውውጥ ከዚያ በኋላ በድሮው መልኩ ሊቀጥል አልቻለም። በቅኝ-ግዛት ዘመን የተቋቋሙት አስተዳደሮች በሙሉ በአፍሪቃ ምድር ውስጥ ቀድሞ የነበሩትን ህብረተሰብአዊ የስራ-ክፍፍልና የንግድ እንቅስቃሴዎች በማኮላሸት አምራቹ ህዝብ ለአውሮፓ ገበያ የሚሆን ጥሬ-ሀብት እንዲያመርት የተገደደበት ፣ ዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍል ነው የተፈጠረው። ከቅኝ አገዛዝ ነጻ መውጣት በኋላ አዲስ የተፈጠረው ዓለም አቀፋዊ የኃይል አሰላለፍ በነጻ ንግድ አማካይነት አሳቦ የድሮ ዐይነት የስራ-ክፍፍል እንዲቀጥል የተደረገበት ነው። ለዚህ ደግሞ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ የተቋቋሙት ዓለም አቀፋዊ ኢንስቲቱሽኖች ሁሉ ፣ እንደ ዓለም ባንክ ፣ እንደ አይም ኤፍና የዓለም ንግድ ድርጅት(WTO) ፣ ይህንን ነጻ ንግድን የሚያጠነክሩና የአፍሪቃን ዕድገት እዚያው ባለህበት እርጋ ሆነው እንዲቀሩ የሚያደርጉ ናቸው። ባገኙትም አዲስ ኃይልና ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ መሳሪያዎችን በመፍጠር ብዙ የአፍሪቃ መንግስታትን ለማሳሳትና የፀረ-ዕድገቱ ዘመን እንዲራዘም አድርገዋል። በዚህ መልክ የተመሰረተው የንግድ ልውውጥና የስራ ክፍፍል በ60ዎቹ ዘመናት የተወሰነ ዕድገት ቢያመጣም ይህ „ዕድገት“ ግን ወደ ውስጥ የቴክኖሎጂ መሻሻልን በመደገፍ የስራ-ክፍፍል ዳብሮ የውስጥ ገበያ ሊያድግ የቻለበት ሁኔታ አይደለም እንዲታይ ያደረገው። በዚህም ምክንያት ይህ ዐይነቱ ዕድገት ዘላቂነት የሌለውና ህብረተሰብአዊ ትርምስ እንዲፈጠር ያደረገ ነው። በዚህ መልክ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ የተመሰረተው አዲሱ የግሎባል ኢኮኖሚ ስርዓት ለአፍሪቃ ዕድገትና ስልጣኔ የሚያመች ሳይሆን አፍሪቃ እዚያው በዚያው ቀጭጫ እንድትቀር ያደረገ ነው። በተለያዩ ጊዜ የወጡትና ተግባራዊ የሆኑት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ሁሉ ወደ ውስጥ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ተደገፈው ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ሀብት እንዳይዳብርና በባህልና በኢኮኖሚ ዕድገት ህብረተሰብአዊ መተሳሰር እንዳይኖር ያደረጉ ናቸው። ዛሬም የሚደረገው ግፊት ፣ ኢትዮጵያንም ሆነ ሌሎች የአፍሪቃ አገሮችን የዓለም ንግድ ድርጅት አባል እንዲሆኑ መገፋፋት በነጻ ንግድ አማካይነት ገበያቸውን ለመውረርና ከውስጥ ደግሞ የማምረት ኃይላቸውን ለማዳከም ነው። በሳይንስና በታሪክ እንደተረጋገጠው ዓለም አቀፋዊ ነጻ ንግድ ሁል ጊዜ የጠነከሩ አገሮችን ነው የሚያግዘው። ከኢኮኖሚ ቲዎሪ አንጻርም እነሱ ብቻ ናቸው በከፍተኛ ቴክኖሎጂ እየታገዙ የምርትን ዋጋ ሊቀነሱና ምርትን ሊያሳድጉ የሚችሉት። በተጨማሪም ልዩ ልዩ ድጎማ ታክሎበት በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ምርትን በርካሽ ዋጋ ለመሸጥና እንደ ኢትዮጵያ የመሳሰሉትን በቴክኖሎጂ ወደ ኋላ የቀሩትን አገሮች የባሳውኑ ማዳከምና ብዙ ህዝብንም ወደ ድህነት መገፍተር የሚችሉት። ለዚህም ከሰባት ዐመት ጀምሮ ሲካሄድ የከረመው የዶሀው ስምምነት እየተባለ የሚጠራው የነጻ ንግድ ውይይት አንድ መቋጠሪያ ሳያገኝ ሊበተን የቻለው ከዚህ ፍራቻ የተነሳ ነው። ውይይቱን ለተከታተለ በጣም ቴክኒካልና ቢሮክራሲየዊ ሲሆን መሰረታዊ የህነን የስልጣኔንና አንድ ህብረተሰብ በነጻ ንግድ አማካይነት እንደ ህብረተሰብ ሊገነባና ነጻ አገር ሊመሰርት ይችላል የሚለው ላይ ያተኮረ አይደለም። በእኔ እምነት እንደዚህ ዐይነቱ ውይይት ጊዜ ማባከኛና መስራት ያለብንን ነገር እንዳንሰራና እንዳናተኩር የሚደረግ አጉል ተንኮል ነው የሚመስለኝ። ሌላው ደግሞ አብዛኛዎቹ የንግድ ስምምነቶች እንደ አስፈላጊነቱ በሁለት አገሮች ሊካሄዱ የሚችሉ ናቸው። እዚህ ላይ ነጻ ንግድ የሚለው ጽንሰ-ሀሳብ ተጣሞ የቀረበና በመሰረቱ እራሱን ዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍልን ጽንሰ-ሀሳብ የሚቃወም ነው። በተጨማሪም በንግድ አማካይነት አንድ ሃገር ማደግ ትችላለች የሚለው ሰበካ ከሳይንሰ ውጭ ነው። ምክንያቱም ከንግድ በፊት ምርት መቅደም አለበት። ለምርት ክንውን ደግሞ የተወሳሰበ የስራ ክፍፍል ያስፈልጋል። አሁን የተያዘው ግፊት ግን አንድ አገር ማምረት የምትችለውንና በዚህ ላይ የሰለጠነችበትን የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚመለከት ሳይሆን ፣ አንድ አገር ራሷ ማምረት የምትችለውን በበቂው ለማምረት ብትችል እንኳ ያንኑ ዐይነት ተመሳሳይ ምርት ወደ ሃገሯ እንድታስገባ ማስገደድና የማምረት ኃይሏን ማዳከም ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ በቂ ስጋ ማምረት ብትችል ወደ ፊት የዓለም ንግድ ደርጅት አባል ብትሆን በብዙ ኬሜካሎች የተበረዘውን የአሜሪካንን የአውሮፓን ስጋ ወደ አገሯ ማስገባት ይኖርባታል ማለት ነው። በሌላ በኩል ግን ለምሳሌ ብዙ አገሮች መኪና እያመረቱ ከሌሎች አገሮች መኪና ያሰመጣሉ። የማምረቻ ዋጋ ቅነሳና ሌሎችም የዲዛይን ነገር የመሳሰሉት ነገሮች ታክለውበት የአንድ አገር መኪና ከሌላው ጋር ሲወዳደር ዋጋው ይቀንሳል። ለምሳሌ ቶዮታ ከጀርመን መኪናዎች ጋር ሲወዳደር በሁለትና በሶስት ሺህ ኦይሮ ይቀንሳል። ስለሆነም ይህንና ሌሎች የቴክኖሎጂ ጉዳዮችንና አስመልክቶ ዓለም አቀፋዊ የንግድ ልውውጥ አስፈላጊ ነው። በሶስተኛው ዓለም አገሮችና በኢንዱስትሪ አገሮች መሀከል ያለው የንግድ ልውውጥ ግን ይህንን ዐይነቱን የዋጋ ልዩነት(Comparative cost advantage) የሚመለከት ሳይሆን በራችሁን ልቀቁና ዝም ብለን ገብተን እንደፈለግን እንጨፍርበት የሚል ነው። ስለሆነም እስከ አሁን

ድረስ በአፍሪቃና በአውሮፓም እንዲሁም በአሜሪካ መሀከል ይደረግ የነበረው የንግድ ልውውጥ አፍሪቃን የሚጎዳና አውሮፓንና አሜሪካንን ደግሞ የሚጠቅም ነው። በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ፣ግብጻዊ ኢኮኖሚስት ፕሮፌሴር ሳሚር አሜንና የፈረንሳዩ ኢኮኖሚስት ኢማኑዓል አግሪሪ እንዳሉት ያልተስታከከል የንግድ ልውውጥ ነው። ሀብት በልዩ ልዩ ዘዴዎች ከአፍሪቃና ከሌሎች የሶስተኛው ዓለም አገሮች የሚሄድበት ዘዴ ነው።

ከዚህ ስንነሳ አፍሪቃ በግሎባል ኢኮኖሚ ውስጥ ያላት ተሳትፎና ከውጭ ወደ ውስጥ የሚገባው መዋዕለ-ነዋይ ይህንን ያህልም የሚያመረቃ አይደለም። ከ70% በመቶ በላይ የሚሆነው የንግድም ሆነ የመዋዕለ-ነዋይ እንቅስቃሴ የሚካሄደው በምዕራብ አውሮፓ ፣ በሰሜን አሜሪካና በጃፓን መሀከል ሲሆን ፣ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የቻይና ተሳትፎና ጥቅም ማግኘት እየጎላ ሊመጣ ችሏል። ያለው ሀቅ ይህ ከሆነ ኢትየጵያ ከግሎባላይዜሽን ምን ጥቅም ታገኛለች የሚለው ሊወሰን የሚችለው 1ኛ) ወደ ፊት በሚከሰተው ዓለም አቀፋዊ የኃይል አሰላለፍና የኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ ቀውስ ሁኔታ ፣ 2ኛ) በሃገር ውስጥ በሚፈጠረው አዲስ የኃይል አሰላለፍና ንቃተ-ህሊና መሰረት ነው። በመሰረቱ ማንኛውም ሃገር በሩን ዘግቶ ሊኖር አይችልም። አሁን ባለው የተሳሰረ ዓለም ሁሉም እንደ አቅሚቲ ያለውን ሸጦ ዶላርም ሆነ ኦይሮ በማግኘት ከውጭ ደግሞ ለዕድገት የሚያመቸውን ማሺኖችና በሃገር ውስጥ ሊመረቱ የማይችሉ የፍጆታ ዕቃዎችን ያስመጣል። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ይህንን በተገደበና በተጠና መልክ ማካሄድ ይቻላል የሚለው ላይ ነው መወያየት የሚያስፈልገው። ከውጭ የሚመጡ ኢንቬስትሜንቶችን ከተመለከትን ለውስጥ ገበያ ዕድገት አመቺ እስካልሆኑና ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ዕድገት አመቺ ሁኔታ እስካልፈጠሩ ድረስ በብዙ አገሮች እንደምናየው ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀልን ነው የሚያመጡት። በተለይም በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች እንደታየው ፣ የዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ዋና ዓላማ የየአገሮችን የውስጥ ገበያ ለማስፋፋትና ቴክኖሎጂያዊ ምጥቀትን ለማምጣት ሳይሆን በርካሽ የሰው ጉልበት ምርት ተመርቶ ለዓለም ገበያ ሊቀርብ የሚችልበትን ሁኔታ ለማዘጋጀት ብቻ ነው። ስለሆነም አብዛኛውን ጊዜ በሶስተኛው ዓለም አገሮች የተተከሉት ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች 1ኛ) ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ግኑኝነት አይመሰርቱም ፤ በሌላ አነጋገር ከውስጥ የሚመረተውን ጥሬ-ሀብት ጠያቂ አይደሉም። በዚህም ምክንያት ለሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ የስራ መስክ በተዘዋዋሪ ሊከፍቱ አይችሉም።2ኛ) ከባንኩ መስክ ጋር ምንም ዐይነት ግኑኝነት አይመሰርቱም ፤ ብድር ወይም ካፒታል ከእናት ኩባንያቸው ነው የሚያገኙት። በዚህም ምክንያት ለባንኩ መስክ ማደግና መስፋፋት ያላቸው አስተዋፅኦ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። 3ኛ) በኩባንያዎች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራው ሰራተኛ በቂ ደሞዝ አይከፈለውም። በቂ ደሞዝ ከሌለው የመግዛት ኃይሉ ደካማ ነው ማለት ነው። የሰራተኛው የመግዛት ኃይል ደካማ በሆነበት ሃገር ደግሞ የውስጥ ገበያ ሊያድግና ሊስፋፋ አይችልም። ስለሆነም መሰረታዊ የሆኑ የመዋዕለ-ነዋይ ህጎች ይጣሳሉ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር በቂ ገቢ የማያገኝ ሰራተኛ ሊገዛም ሊቆጥብም አይችልም ማለት ነው። ቁጠባው ዝቅ ያለ ከሆነ ባንኮች የሚያበድሩት በቂ ካፒታል አይኖራቸውም ማለት ነው። ይህ ጉዳይ በዕቃና በገንዘብ መሀከል የሚኖረው ግኑኝነት ተስተካክሎ እንዳያድግ ያግዳል ማለት ነው። የገንዘብም መሽከርከር (Velocity of Money) ዝቅተኛ ስለሆነ ገንዘብ ወደ ካፒታልነት ለመለወጥ ያለው ዕድል በጣም ደካማ ይሆናል ማለት ነው። 3ኛ) የውስጥ ገበያ ሊስፋፋ በማይችልበት ቦታ ደግሞ ከተማዎች ሊያድጉ በፍጹም አይችሉም። ከተማዎች በማያድጉበትና በማይስፋፉበት ቦታ ደግሞ ባህል ሊያብብና በህዝብ ዘንድ መተሳሰር ሊኖር በፍጹም አይችልም ማለት ነው። በአንጻሩ እዚህና እዚያ የሚተከሉት ኢንዱስትሪዎች ህብረተሰብአዊ መዘበራረቅንና የባህል መበላሸትን ያስከትላሉ። በዚህም ምክንያት ጤናማው የሰዎች የማሰብ ኃይል በመበላሸት ወደ አልባሌ ቦታ በመውደቅ የታሪክ ባለቤት እንዳይሆኑ ይደረጋሉ። 4ኛ) አብዛኛዎች ኩባንያዎች የገቢ ታክስ አይከፍሉም። በተለያዩ ዘዴዎች የማምረቻውን ዋጋ በመቆለል(Transfer price mechanism) ትንሽ ትርፍ ያተረፉ በማስመሰል ወደ ሃገራቸው እንዲተላለፍ ያደርጋሉ ማለት ነው።4ኛ) ከፖለቲካው መስክ ጋር በመቆላለፍ ወደ ውስጥ የጭቆና መሳሪያ እንዲጠናከርና የሰራተኛው መብት እንዲረገጥ በማድረግ ዲሞክራሲያ ባህል እንዳይዳብር እንቅፋት ይሆናሉ ማለት ነው። በ60ዎቹና ከዚያ በኋላ በብዙ የላቲንና የአፍሪቃ አገሮች የተስፋፉት የጭቆና አገዛዞች ከዓለም አቀፍ ኩባንያዎችና ከአሜሪካን የበላይነት ጋር በጥብቅ የተያያዙ ናቸው። ስለሆነም ስለግሎባላይዜሽን ጠቃሚነትም ሆነ ጎጅነት በሚወራበት ጊዜ እነዚህ ነገሮች በጥብቅ መጠናትና ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለባቸው።

እንደ ኢትዮጵያ የመሰለች ደሀ ሃገር አሁን ካለችበት ሁኔታ እንዴት መላቀቅና የተከበረን ቦታ ትይዛለች የሚለው በአንድ ገጽ የሚመለስ ጉዳይ አይደለም። ማለት የሚቻለው በኛም ሆነ በብዙ የአፍሪቃ አገሮች ዕድገትንና ስልጣኔን በሚመለከት የተሳሳተ ግምት አለ። ብዙዎች ስለ ዕድገት የሚያትቱ የኢኮኖሚ መጽሀፎች በተሳሳተ መልክ

ስለቀረቡ ብዙዎችን አሳስተዋል። በሌላ አነጋገር ዓለም አቀፍ የስራ ክፍፍልን ማዕከላዊ ቦታ በመስጠት ነው ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማተት የሚጀምሩት። ይህ ደግሞ ዕውነተኛውንና የተወሳሰበውን የካፒታሊዝምን ዕድገት እንዳንረዳ ያደርጋል። ለምሳሌ ፕሮፌሰር ካርል ፖላኒ የጻፉትን The Great Transformation ም ሆነ የማርክስን ዳስ ካፒታል ላነበበ እነዚህ ስራዎች ሙሉ በሙሉ ዩኒቨርሲቲ ከምንማረውና ከምናስተምረው የኢኮኖሚ ዕድገት ትምህርት ጋር ይቃረናሉ።እንደዚሁም የነጻ ንግድን ተቃውሞ በግሩም መልክ የቀረበውን የፍሪድሪሽ ሊስትን መጽሀፍ ላነበበ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚረዳው ሌላ ነገር ነው። ስለዚህም የኢኮኖሚ ዕድገት ከታሪክ ጋር ተነጻጽሮ ካልቀረበ ብዙ የዋህ ሰዎችን ያሳስታል። በተለይም የነ ፓውል ክሩግማንንና የሚካኤል ቶዳሮን የኢኮኖሚ መጽሀፍ ያነበበ ወደ ተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ይደርሳል ።

ወደ ተጨባጩ ጉዳይ ከመጣን ለማንኛውም የኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ጥያቄ የፖለቲካ ሁኔታ መፈታት ነው። ጨቋኝ ስርዓት በሰፈነበት ፣ የዲሞክራሲ መብት በታፈነበትና ዲሞክራሲያዊ ኢንስቲቱሽኖች በሌሉበት ሃገር ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት ያስቸግራል። በተለይም ለአንድ ሃገር ዕድገት የዲሞክራሲያዊ ኢንስቲቱሽኖች መኖር ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ የሚያግዝን ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ዕድገት የሚያመች የትምህርት ስርዓት መዋቀር አለበት። ለአንድ ሃገር ህብረተሰብአዊ ዕድገት ዕውቀት ቁልፍ ነው። ለምሳሌ ብዙም ጥሬ ሀብት ሳይኖራቸው ከፍተኛ ዕድገትን የተጎናፀፉ አገሮች ፣ ጀርመን ፣ ጃፓንና ደቡብ ኮሪያ የዕውቀትን መሰረታዊ ቦታ በመረዳት ነው። የአንድ አገር ህዝብ ጭንቅላቱ ሲዳብርና የማሰብ ኃይሉ ከፍ ሲል አንድን ተጨባጭ ነገር ወደ ልዩ ልዩ ጠቀሜታ ወደ ሚሰጡ ነገሮች መለወጥ ይችላል። ለምሳሌ ከሰሊጥ ዘይት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ለምግብ የሚገለግሉ ነገሮችንም መስራት ይቻላል። ከወተት ከቅቤ ባሻ ገር ልዩ ልዩ የቺዝ ዐይነቶች መስራት ይቻላል። ስለሆነም ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ስናወራ ፣ በቴክኖሎጂና በሳይንስ ላይ የተመሰረተ የካፒታሊዝም ዕድገት ወይንስ በነጻ ገበያ ላይ የተመሰረተ ዝርክርክ የንግድ ልውውጥ መሀከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ለመጀመሪያው የምንታገል ከሆነ የመንግስት ሚና ከፍተኛ ቦታን እንደሚይዝና የመጀመሪያው ተግባር የውስጥ ገበያን ለማዳበር የጥሬ-ሀብትንም ሆነ ሰውን ኃይል በከፍተኛ ደረጃ ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ባለፉት 60 ዐመታት በምዕራብ የካፒታሊስት አገሮችና በኢንስቲቱሽናቸው የሚደረግብን ጫና ያለንን የሰው ኃይል በተቀነባበር መልክ እንዳናቀሳቅስ ነው። ታሪክ እንደሚያረጋግጠው ደግሞ የሰው ኃይል ለኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል። ካፒታል ደግሞ የሰው ልጅ የስራ ውጤት ነው። ስለዚህም ካፒታልን እንደዋናው አንቀሳቃሽ ኃይል አድርጎ መውሰድ ከፍተኛ ስህተት ነው። ስለዚህም በአንዳንዶች ገንዘብ ወይም ካፒታል የለንምና ስለዚህም ማደግ አንችልም የሚለው የተሳሳተ አቀራረብ አደገኛና ወደ ቁም ነገሮች ላይ እንዳናተኩር የሚያደርገን ነው።

ባጭሩ የኢትዮጵያ  ዕድገት ሊወሰን የሚችለው ከውጭ በሚመጣ የመዋዕለ-ንዋይ ኃይል ሳይሆን በእኛ በማያቋርጥ ታታሪነትና ዕምነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። ስለሆነም አስተሳሰባችን በተወሰኑ ቁም ነገሮች ላይ መሰብሰብ አለበት። የመጀመሪያው ህብረተሰብ ማለት ምን ማለት ነው። ሁለተኛው ፣ አንድን ህብረተሰብ እንደ ህብተረተሰብ እንዲገነባና ወደ ፊት እንዲተላለፍ ምን ምን ቅድመ-ሁኔታዎች መጣል አለባቸው። ሶስተኛው ፣ የብሄራዊ-ነጻነት ጉዳይና የራሳችንን ዕድል ራሳችን የመወሰኑ ጉዳይ በሰፊው መታየት አለበት። አራተኛው ፣ ለአንድ ደርጅት ከሚኖረን ፍቅር ይልቅ ለህዝባችንና ለሃገራችን የሚኖረንን ፍቅርና ኃላፊነት ማስቀደም። የሰላሳ ዐመቱን የአብዮት ታሪክ ለተመለከተ ደርጅቶችን እንደ ርዕዮተ-ዓለም ማየትና የኔ ድርጅት ስልጣን ካልያዘ አገር ነጻ ልትወጣ አትችልም የሚለው አስተሳሰብ በጣም ጎልቶ ይታያል። የብዙዎን አስተሳሰብና ጽሁፍ ለተመለከተ ከሳይንስ ጋር የሚጣጣም አይደለም። አምስተኛው ፣ መቻቻልን ማስቀደምና የሌላውንም ሃሳብ ለማዳመጥና ለማክበር መሞከር። ስድስተኛው ፣ ክሪቲካል አመለካከትን ማዳበር። በነዚህ መሰረተ-ሃሳቦች ላይ ከሰራንና ከቡድናዊ ስሜት ተላቀን የኢትዮጵያዊነትን ስሜት ከሳይንስ አንጻር ማደበር ከቻልን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማደግና በምግብ ራሳችንን  የማንችልበት ምክንያት በፍጹም አይታየኝም።

<u>*ማሳሰቢያ*</u>: እንዳንድ ቃሎችን እንዳብራራ ስለተጠየኩኝ ማባራሪያዎች የሚከተሉት ናቸው።

Acquisition +Merging= የመጀመሪያው አንድ ኩባንያ ሌላውን ሲገዛ ሲያመለክት ፣ ሁለተኛው በሁለት ኩባንያዎች መሀከል የሚደረግ ውህደትን

ያሳያል። ከዘጠናኛው ዓ.ም ጀምሮ እየተጠናከረ የመጣ የመዋሀድና አንዱ ሌላውን የመዋጫ ዘዴ ነው።

Arbitrage= በሁለት ካረንሲዎች ወይም በወለድ መሀከል የሚፈጠር ልዩነት። ለምሳሌ የዶላር ዋጋ ዝቅ በሚልበት ጊዜ ዶላርን ገዝቶ ዋጋው ከፍ ሲል ይሸጣል ፤በጊዜ ምክንያት የሚፈጠር የዋጋ ልዩነት አርቢትራዥ ይባላል። ሌላው ምሳሌ አሜሪካን ካፒታል ገበያ ላይ ወለዱ ከፍ ሲል የአውሮፓ ከበርቴዎች ሀብታቸውን ከፍ ካለው ወለድ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ አሜሪካ ኢንቬስት ያደርጋሉ።በአውሮፓና በአሜሪካ ያለው የወለድ ልዩነት አርቢትራዥ ይባላል።

Credit Worthy= ለብድር ብቃትነት መኖር

Debt Reschudling = ለምሳሌ አንድ ሃገር የተበደረችውን ብድር በጊዜው መክፈል ካልቻለች በአይ ኤም ኤፍ ኣማካይነት ተጨማሪ ብድር ካበደራት ባንክ በመበደር ብድሩን እንድትከፍል ትገደዳለች። ይህ ዘዴ የብድሩን መጠን ከፍ ሲያደርግ ፣ ተበዳሪዋ ሃገር ያልተከፈለው ወለድ ላይ ተጨማሪ ወለድ በመክፈል በዕዳ እንድትተበተብና ወደ ውስጥ ከምታመርተው አብዛኛው ክፍል ወይም ከውጭ ንግድ ከምታገኘው ካረንሲ አብዛኛውን በመክፈል ኢኮኖሚዋን ለማሳደግ ያላት ኃይል እየመነመነ እንዲመጣ ያደርገል። ከ1982 ጀምሮ በሜክሲኮ ፣ በብራዚልና በአርጀንቲና የተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ እነዚህ አገሮች በዚህ ዐይነቱ የዕዳና የወለድ አከፋፈል ዘዴ ስለተበተቡ ነው።

Derivatives= ይህ ዐይነቱ ዘዴ ከነበሩ ገበያዎች ፤ለምሳሌ ከዳው ጆን ኢንዴክስ ወይም ከጀርመን የስቶክ ገበያ የሚተነተንና በአንድ ድርሻ ላይ የሚመካ መሆኑ ቀርቶ ከተጠቃለሉ(indicies) የሚፈልቅና በዚህም አማካይነት በሚፈጠረው ዝቅና ከፍ ማለት የሚገኝ ትርፍ ነው። በዚህ መልክ የሚካፈሉት ባላሀብቶች ዝቅና ከፍ ይላል ብለው በመወራረድ ነው። በዚህ ዐይነት ውድድር የሚሳተፉት ብዙ ገንዘብ ያላቸውና የገበያውንም ዘዴ ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው።

Exteranlities= ከፋብሪካ የሚወጡ አካባቢን የሚበክሉ ቆሻሻዎች ግን ደግሞ ለማስወገድ የህብረተሰብ ሀብት የሚፈስባቸው ናቸው። አሁን አሁን በብዙ የኢንዱስትሪ አገሮች ባለው የቴክኖሎጂ ምጥቀት የማጣሪያ ዘዴ ቢኖርም በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የመተከሉት ኢንዱስትሪዎች  አካባቢዎችን እያቆሸሹና ጤንነትን እያቃወሱ ነው።

Financial Market= ገንዘብና ገንዘብ-ነክ የመሳሰሉ በመሰረቱ ትርፍም ሆነ ወለድ የሚገኝበት የገበያ ልውውጥ ነው። ካረንሲዎች ፣ የመንግስት ወረቀቶችና(Securities, bonds) የግል ባለሀብቶች ተጨማሪ ካፒታል ለማግኘት ሲሉ የወረቀት ማረጋገጫ(Stocks, Obligations etc.) የሚሸጡበት ገበያ ነው።

Primary Market= የመንግስት ወይም የኢንዱስትሪ ሰርተፊኬት ወይም ክፍያ ገበያ ላይ መጀመሪያ ለሺያጭ ሲቀርብ ፤ይህ የመጀመሪያው ገበያ ይባላል። በመሰረቱ መንግሰትም ሆነ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች ሰርተፊኬት ገበያ ላይ አውጥተው የሚሸጡት ፣ መንግስት ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ ሲሆን ፣ የኢንዱስትሪ ከበርቴዎች ደግሞ ከባንክ ከመበደር ይልቅ በዚህ አማካይነት ለተጨማሪ መዋዕለ-ነዋይ ካፒታል ስለሚያገኙ ሰርተፊኬቶችን ገበያ ላይ በማውጣት የገንዘብ ሀብት ያለው የትርፍ ተካፋይ እንዲሆን መንገድ ያመቻቻሉ። ይህ ቀናውና ቀጥተኛው መንገድ ነው።

Real Economy= የሚዳሰስ ፣ የሚታይና የሚለካ ሲሆን ፣ በመሰረቱ በማሽኖች ፣ በባቡር ሀዲድ ፣ በመንገድ ስራ ፣ በውሃ-ፍሳሽ ስራ ፣ በትምህርት ቤቶች ስራ የሚገለጸው ተጨባጭ ኢኮኖሚ ይባላል። በፊናንስ ገበያ

ላይ የሚደረገው ልውውጥ ቶሎ ቶሎ ትርፍ(speculation) የማግኘት ባህርይ ሲኖረው ፣ በተጨባጩ የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ የሚውለው መዋዕለ-ነዋይ ትርፍ ሊያመጣ የሚችለው ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው።

Secondary Market= ይህ ዐይነቱ ገበያ የቁማር መጫወቻ ነው ብሎ መናገር ይቻላል። በመጀመሪያው ገበያ ላይ የተሸጠው ሰርተፊኬት ወይም የኢንዱስትሪ ክፍያ (Bonds, Stocks etc.) በባንኮች ወይም በሌላ ተወካይ አማካይነት ወረቀቱ ከአንዱ እጅ ወደ ሌላው እንደገበያው ዝቅና ከፍ ማለት ይተላለፋል። ይህ በየሰዓቱና በየዕለቱ ከፍና ዝቅ የሚል የቁማር ጫወታ ሲሆን ከተጨባጩ ኢኮኖሚ ዘርፍ ጋር ምንም ግኑኝነት የለውም። የኢንቬስተሮች ገቢ በየዕለቱ የሚከሰተው የሽያጭ ወይም የዋጋ ልዩነት ነው።

Securitization = ግለሰቦች ከባንክ ተበድረው ቤት ይሰራሉ ወይም ይገዛሉ። ባንኩ ተባዳሪው መክፈል የማይችል መስሎ ከታየው ዕዳውን ለሌላ ኢንቬስተር ይሸጣል። ግኑኝነቱ በባንኩና በተበዳሪው መሀከል መሆኑ ቀርቶ በአዲሱ ኢንቬስተርና በተበዳሪው መሀከል ሲሆን ፣ ኢንቨስተሩ ወለዱን ከፍ ሊያደርገበት ይችላል ወይም ደግሞ ቤቱን አሳድሶ ለሌላ ሰው ሊሸጠው ይችላል። ይህ ዐይነቱ ብድርን የማረጋገጫ ዘዴ ብዞዎችን ካለቤት አስቀተርቷል።

Shareholder Value = ከኢንዱስትሪ ክፍያ(stock) የሚገኝ ድርሻ ወይም ዋጋ ነው። በአሁኑ ወቅት አይሎ የሚታይ በተለይም ማኔጀሮች የሚጠቀሙበት ዘዴ ሲሆን ገንዘባቸውን አፍሰው ትርፍ እናገኛለን ብለው የሚጠባበቁትን ባለሀብታሞች የሚጠቅም ነው። በዚህም ምክንያት ልዩ ልዩ የዋጋ ቅነሳ ስትራቴጂ ይከተላሉ። ለምሳሌ ሰራተኞችን መቀነስ።

Subprime= ይህ ጽንሰ-ሃሳብ የሚያመለክትው የራሳቸው መደገፊያ ሀብት ወይም ተከታታይ የወር ገቢ ሳይኖራቸው ብድር በመታለል ወይም በግዳጅ መልክ እየተበደሩ ቤት የሚገዙትን የሚመለከት ሲሆን ፣ የተፈጠረውም አሜሪካ ነው። የዚህ ብድር ሰለባዎች ብዙም ዕውቀት የሌላቸው ጥቁር አሜሪካኖችና ላቲኖች ናቸው። እነዚህም „Ninija“ በመባል ይታወቃሉ። No income, no job or no assets ማለት ነው። በዐይነቱ ዝቅተኛ የብድር ዐይነት በመባልም ይታወቃል። የማዕከላዊ ባንክ ለንግድ ባንኮች ከሚሰጠው የብድር ወለድ(prime rate) በታች የሚሰጥ ስለሆነ በዚህም ምክንያት ዝቅተኛ ይባላል።

Value added= በምርት ሂደት ውስጥ የሚገኘው ተጨማሪ ምርት ወይም ትርፋማው የምርት ክፍል ነው። በተጨማሪ አንድ ጥሬ-ሀብት ከጥሬነቱ ተላቆ ለጠቀሚታ ወይም ለፍጆታ ሲለወጥ ይህ ዐይነቱ የምርት ሂደት ተጨማሪ ዋጋ ወይም ምርት አስገኘ ማለት ይቻላል።ከዕውነተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት አኳያ ትርፍ ምርት ሊገኝ የሚችለው የምርት ክንውን በሳይንስና በቴክኖሎጂ ሲደገፍ ሲሆን ፣ ይህ በራሱ ደግሞ በየጊዜው በሚሻሻል ዕውቀት መደገፍ አለበት። አንዳንድ ኢኮኖሚስቶች እንደሚሉት ጽንሰ-ሃሳቡ የሚያመለክተው እርስ በርሱ የተያያዘን የአመራረት ዘዴንና አንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ በሌላው ላይ ሲመካ እንደሰንሰለት የተያያዘ( Value added chain) የምርት ክንውንን የሚያመለክት ነው።

ፈቃዱ በቀለ